አሐዱ:ባንክ Ahadu Bank
ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation
ahadubank.com

ይቻላል
It's Possible!

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ.
Tsehay Insurance S.C.
ፀሐይ ለሁሉም ታበራለች!!
The Sun Shines For All !!
ቦሌ ድልድይ ከብራስ ሆስፒታል ፊትለፊት
Bole Bridge, in front of Brass Hospital
Tel.+251 111 11 97 70/71 +251 111 11 98 27/97 93
Fax: +251 111 11 98 86
Website: www.tsehayinsurance.com
E-mail: marketingd@tsehayinsurance.com

# ንግድና ልማት

የካቲት 2016 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com

## አዲስ ቻምበር አለምአቀፍ የሴቶች ቀንን በፓናል ውይይት አከበረ

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**



አለምአቀፉ የሴቶች ቀን በየአመቱ ማርች 8 በመላው አለም የሚከበር ሲሆን የሴቶች የኢኮኖሚ የፖለቲካና የሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ መንግስታት ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበረሰብ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በሴቶች ዙርያ የገቡትን ቃልኪዳን የሚፈትሹበት እለት ነው:: ይህ እለት በአለምአቀፍ ደረጃ በበርካታ ሀገራት በዚህ በያዝነው የመጋት ወር እየተከበረ ሲሆን በኢትዮጵያም በመንግስት ደረጃ እና በተቃማት ደረጃ ተከብራል:: ከቅርብ አመታት ወዲህ አዲስ ቻምበር አለምአቀፉን የሴቶች ቀንን በተለያዩ ዝግጅቶች የሚያከብር ሲሆን በዚህ አመት የተከበረውን የሴቶች ቀን በፓናል ውይይት አክብራል:: ሴቶች በማምረቻው ዘርፍ በሚል መሪ ቃል በአዲስ ቻምበር የተዘጋጀው የውይይት መድረክ በቢዝነስና አመራር ስኬታማ ሴቶች የተገኙበት እና ልምዳቸውን ያካፈሉበት መድረክ ነበር:: በዚህ የፓናል ውይይት ላይ ሴት ሥራ ፈጣሪዎችን ይበልጥ የሚያበረታቱ የፖሊሲ እርምጃዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ ጥሪ ቀርባል::

በዚህ የፓናል መድረክ ላይ የም/ቤቱ ፕሬዝደንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ባስተላለፉት መልዕክት በአገራችን ታሪክ ሴቶች በኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ እንዲሁም ተጠቃሚነት በጣም አናሳ ነው ያሉ ሲሆን ሴቶች በኢንቨስትመንት እና በሥራ ፈጠራ ላይ በስፋት እንዳይሳተፉ ማነቆ ከሆኑት ተግዳሮቶች መካከል የብድር አቅርቦት ችግር አንዱ ነው ብለዋል:: በተለይ በማኑፋክቸሪንግ ላይ የተሰማሩ ሴቶች በብዙ ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ እንደሚገኙ ገልጸዋል::

መንግሥት ተተኪ ምርቶችን ለሚያመርቱ እና የውጪ ምንዛሬ ለሚያስገኙ ማምረቻዎች ትኩረት መስጠቱ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ሴቶች በማንዩፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ያላቸውን አነስተኛ ተሳትፎ ለማሳደግ በሴቶች ላይ ያተኮሩ ፖሊሲዎችን በመፈተሽ ማበረታቻዎቸን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ፕሬዝደንቷ አሳስበዋል::

በዝግጅቱ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽነር ወ/ሮ ሃና አርአያሥላሴ በበኩላቸው መንግሥት በአገር በቀሉ የኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ውስጥ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን በማመን የግሉ ዘርፍ በስፋት እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል:: በተለይም ሴቶች በአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ መንግሥት የተለያዩ የሕግ እና የፖሊሲ እርምጃዎችን ወስዷል ብለዋል:: ነገር ግን የሴቶች በኢንቨስትመንት በተለይም በማንዩፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ያላቸው ተሳትፎ በጣም አነስተኛ መሆኑን አሰታውሰው ይህንን እውነታ ለማሻሻል ኮሚሽን መ/ቤታቸው አዲስ ቻምበርን ጨምሮ ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በትብብር ለመሥራ ዝግጁ ነው ብለዋል::

በሥነስርዓቱ ላይ ስኬታማ የሆኑ ሴት የቢዝነስ መሪዎች እና ሥራ ፈጣሪዎች ወረቀት ያቀረቡ ሲሆን በተለይ ሴቶችን በሥራ ፈጠራ እና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ዙሪያ ያሉ ዕድሎች እና ተግዳሮቶችን እንዲሆኑም ማነቆ የሆኑ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች የጠቆሙ ሲሆን የመፍትሔ ሃሳቦችንም ሰንዝረዋል::

ከተሳታፊዎች ጥያቄዎች እና አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን በአቅራቢዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥቷል:: አዲስ ቻምበር የዘንድሮውን የዓለም ሴቶች ቀን 'Women In Manufacturing' በሚል መሪ ሃሳብ ማክበሩን ለማወቅ ተችሏል::

አዲስ ቻምበር ADDIS CHAMBER
Forum For ExEcutive Leaders
FEEL
SAK TRAINING AND CONSULTANCY Since 2005
Leadership and Achievement Mindset



Kebour Ghenna
Former President of Addis Ababa Chamber of Commerce and Ethiopia Chamber of Commerce
Executive Director of Initiative Africa and Pan-Africa Chamber of Commerce and Industry

April 2, 2024
5:00 pm-7:30 pm
Location:
Inter Luxury Hotel



Moderator
Dr. Adera Abdela

Entrance Fee:
3500/per person

For Registration
0911194965
0911514422
0911343078

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**፶ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirmamecha@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
ከፍያለው ዋሲሁን
ካሳሁን ማሞ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ስዩም ጫኔ-ሰብሳቢ
ካሳሁን ማሞ - አባል
አሸናፊ ምትኩ - አባል
አቶ ደሳለኝ ደጀን - አባል
አቶ የሀንስ ወ/ገብርኤል - አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
የካቲት 2016 እትም

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# ርዕሰ አንቀጽ

## ሴቶችን በማበረታታት ጤናማና አምራች ዜጋ በማድረግ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እኩልነት የማረጋገጥ አስፈላጊነት!

አለማችን በፈጠራ፣ በሳይንስ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ዘርፍ ላይ የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግ በአገር ግንባታ ሂደት የላቀ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ እንደሚገባ ዘወትር እየተገለፀ መሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ሀቅ ነው::

የሥራ ዕድል ፈጠራ ደግሞ ከኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ተነጥሎ የማይታይ በመሆኑ ዘርፉን አገራዊ አጀንዳ በማድረግ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ስራ መሰራት አለበት::ሴቶችና ወጣት ዜጎች ስራ እንዲፈጥሩና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል አዲስ ቻምበር አበክሮ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል:: ለዚያም ሲባል ሴቶች የኢኮኖሚ አቅማቸው በስራ ፈጠራ ረገድ እንዲጎለብትና የንግድ ተወዳዳሪነታቸው እንዲያድግ እየተከናወኑ የሚገኙ በርካታ ስራዎች አሉ:: በእርግጥ ሴቶችና የስራ እድል ፈጠራ በጥናት ላይ የተመሰረተና ማምረትን ማእከል ያደረገ ካልሆነ የታለመለትን አላማ ማሳካት አይቻልም::

በዚህ ረገድ ለስራ ፈጠራና ኢንቨስትመንት ማነቆ የሆኑ አሰራሮችን በመፍታት ሴቶች በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ስራ ፈጣሪነትን ባህል እንዲያደርጉት መስራት የሁላችንም ድርሻ ነው:: አሁን አሁን በሀገራችን በሴቶች ጉዳይ ላይ የታየው ዕድገት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቢሆንም ሴቶችን በአመራርና በኢኮኖሚ ረገድ ማብቃትና እኩልነታቸውን በማረጋገጥ ረገድ ሥራው ተጠናቋል ተብሎ አይታሰብም :: ሥራው ተጀመረ እንጂ መድረስ የሚገባው ጫፍ ላይ አልተደረሰም::

ሁሉም ወገን ሴትን ማበረታታት ካልቻለ ፤ ጤናማና አምራች ካልተደረጉ ስለ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እኩልነት ማለሙ ብዙም ትርጉም የለውም::
ለሴት የነጻነቷ ቁልፍ እድል እንድታገኝ መደላድሉን መፍጠር ነው:: ብዙ የሆኑ ችግሮችን በመቅረፍ እና በማለፍ እንዲሁም ለሌሎች እህቶችና ወንድሞች የስራ እድልና ገቢ ምንጭ የሆኑ ጀግና እና ተምሳሌት ሴቶችን መፍጠር የግድ ይሆናል:: ስለሆነም የተለያየ የፖሊሲ ድጋፎችን ተጠቅሞ በቀጥታ ሊደረስላቸው ስለሚገባ በዚህ ዙሪያ ተባብሮ መስራት አስፈላጊ ይሆናል::

በጥቅሉ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማሩ ሴቶች የስራ ፈጠራ ችግሮቻቸውን ከፖሊሲ፣ ከአደረጃጀትና ከኩባንያዎች ከራሳቸው ሊመነጭ የሚችል በመሆኑ እነዚህን ችግሮች መፍታት ሴቶች በስራ ፈጠራና በአገሪቱ ዕድገት የሚገባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ያስችላል :: በአጠቃላይ የሀገራችን ስራ ፈጣሪ ሴቶች አቅማቸው ሊጠናከር እንደሚገባና መንግሥስትን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት በዚህ ላይ ትኩረት ማድረግ ለነገ የሚባል አይደለም ::

ንግድ ምክር ቤታችንም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩ ስራ ፈጣሪ ሴቶችን በማነቃቃት፣ አቅማቸውን በእውቀት በመገንባት እንዲሁም የህይወት እና የሥራ ምርጫቸው የተሻለ እንዲሆን የፖሊሲ ማሻሻያና ዘላቂ የግንዛቤ ሥራዎችን በማከናወን ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ አሁንም በርትቶ ይሰራል::

# በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ድልደይ ፊት ለፊት የሚገኙ አስራ ሁለት ሱቆች ለመንገድ ማሰፈፊያ በሚል የለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይፈረሱ መባሉ እንዳሳዘናቸው ነጋዴዎች ገለፁ ፡፡





**በከፍያለው ዋሲሁን**

በቦሌ አየር መንገድ ፊት ለፊት የሚገኙት ባለ አንድ ፎቅ የንግድ ቤቶች ፣ፋርማሲዎች ፣ ካፌዎች እና በንግድ አግልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎች የስራ ቦታቸው እንዲፈርስ እየተደረገ መሆኑ ትክክል እንዳልሆነ በአካባቢው ሱቆችን ተከራይተው የሚሰሩ እና የንግድ ቤት ባለቤቶች ለአዲስ ቻምበር ሚዲያ ተናግረዋል፡፡ የአዲስ ቻምበር ሚዲያም በአካል በቦታው በመገኘት ለመመልከት ችሏል፡፡ ቅሬታ አቅራቢዎቹ ቦታው ለልማት መፈለጉ እንዳለ ሆኖ በአስቸኳይ ይፍረሱ መባሉ እና በአጭር ቀነ ገደብ ውስጥ መሆን አልነበረበትም ብለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ግለሰቦች ለዘመናት ለፍተው ያፈሯቸው ንብረቶቻውን በምን ሁኔታ እንደሚለቁ እና እንደሚያፈርሱ ግልጽ ሳይደረግ ድርጊቱ መፈጸሙ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት

ይዞታ የሚለቀቅበትና ካሳ የሚከፈልበት ሁኔታን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ሊጻረር የሚችል አካሄድ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ከቅሬታ አቅራቢዎቹ መካከል ነጋዴውና የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የቦርድ አባል አቶ አበራ አበጋዝ ልማት መኖር የለበትም እያልን አይደለም ብለዋል ፡፡ ይሁንና የንግድ ሱቆች በመፍረስ ሂደት የሚገኙ ጥቅሞችና ጉዳቶች በአዋጁ መሰረት ልናውቅ የሚገባ እና ይህንን ሳይነግሩን ወደ ፈረሳ መገባቱ አግባብነት የለውም ብለዋል ፡፡

የንግድ ማህበረሰብ ድምፅ የሆነው የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የተቋቋመው የንግድ ህብረተሰብን ጥቅምና ፍላጎት ለማስከበር መሆኑን ጠቁመው ይህንን ጉዳይ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ንግድ ምክር ቤቱ ያለውን ክፍተኛ ተሰሚነት ለወረዳውም ፣ ለክፍለ ከተማው እንዲሁም ከንቲባ ጽ/ቤት በማሳወቅ ድምፃቸውን እንዲያሰማለቸው ጠይቀዋል ፡፡

# ንግድ ም/ቤቱ የኩባንያዎች የብድር መመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት/የክሬዲት ሬቲንግ/ ጥቅምን ለአባላቱ አስተዋወቀ። አዲሱ አገልግሎት የንግዱ ሕ/ሰብ ብድር ለማግኘት ያለበትን የቆየ ችግር ይቀርፋል ተብሏል!




**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

የክሬዲት ሬቲንግ አገልግሎት በዓለም ላይ የተለመደ አሰራር ሲሆን አገልግሎቱም የቢዝነስ ኩባንያዎች ለብድር ብቁ መሆናቸውን በተቀመጡ መመዘኛዎች አማካኝነት በማጣራት እና ሰርተው ብድር የመመለስ ብቃት እንዳላቸው ለአበዳሪ የፋይናንስ ተቋማት ማረጋገጫ በመስጠት ነጋዴዎች የብድር አገልግሎት በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያስችል መሳርያ ነው፡፡

ይህን አዲስ አገልግሎት ለማስተዋወቅ በተዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ላይ የንግድ ም/ቤቱ ፕሬዝደንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ብድር ማግኘት ከፍተኛ ውጣ ውረድ የሚጠይቅ እና ለአመታት የነጋዴው ዋነኛ የዕድገት ማነቆ ሆኖ ቆይቷል ብለዋል፡፡

ታዲያ ንግድ ምክር ቤቱ ያስተዋወቀው ይኸው አገልግሎት ለንግዱ ሕብረተሰብ የክሬዲት ሬቲንግ አገልግሎት በመስጠት ነጋዴው ያለበትን የብድር የማግኘት ችግር ለመቅረፍ ያስችላል ብለዋል፡፡ የክሬዲት ሬቲንግ አገልግሎት በአበዳሪ ባንኮች እና በተበዳሪ ኩባንያዎች መካከል መተማመን እና ዘላቂ ትብብር እንዲኖራቸው ትልቅ ድርሻ አለው ሲሉ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የአዲስ ቻምበር ዋና ጸሐፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በበኩላቸው ንግድ ምክር ቤቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዘመኑ የሚጠይቀውን አዳዲስ አገልግሎቶችን ለንግዱ ሕብረተሰብ ማቅረብ መጀመሩን ገልጸው፤ የዳይሬክተሮች ተቋም እና የጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል ( BIC) ለአባላቱ እና ለመላው የንግድ ሕብረተሰብ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ለአብነት አንስተዋል፡፡ ንግድ ምክር ቤቱ በተለይ አዲሱን የክሬዲት ሬቲንግ አገልግሎት ከድርሻ ገበያ ጋር ተያይዞ ለአባላቱ ለመጀመር ተቀማጭነቱ ዱባይ ከሆነው ኢንተርናሽናል ክሬዲት ሬቲንግ አጀንሲ (ICRA) ጋር በትብብር ለመሥራት የመግባቢያ ሰነድ ቀደም ሲል መፈራረሙን ገልጸዋል፡፡ መንግስት የጀመረውን የፋይናንስ ሪፎርም ተከትለው የተቋቋሙት እንደ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን እና የሴኪዩሪቲ ኤክስቼንግ ያሉ መስሪያ ቤቶች ተልዕኮአቸውን ማስፈጸም የሚችሉት የክሬዲት ሬቲንግ አገልግሎት ሰጪ ተቋም መኖር ሲችል ብቻ ነው ያ ሲሆን ስለዚህ አዲስ ቻምበር ተነሳሽነቱን አስቀድሞ መጀመሩን ዋና ጸሀፊው አክለው ገልጸዋል፡፡

ንግድ ምክር ቤቱ የንግዱን ሕብረተሰብ አቅም በመገንባት ብቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆን ዘመኑ የሚጠይቀውን አገልግሎት ለማቅረብ ዝግጁ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በዝግጅቱ ላይ ስለ ክሬዲት ሬቲንግ አገልግሎት ፅንሰሃሳብ፤መርሆች፤ የአተገባበር ስልቶች እና የአገራት ተሞክሮዎች በተለያዩ ምሑራን ገለጻ የተደረገ ሲሆን ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

# አዲስ ቻምበር “የሥራ መሪዎች መድረክ” አገልግሎትን በይፋ ጀመረ




**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

“የሥራ መሪዎች መድረክ” (Executive Leaders Forum) የተሰኘው ንግድ ም/ቤቱ ያስጀመረው አገልግሎት አንጋፋ የቢዝነስ መሪዎች ዕውቀታቸውን እና ያለፉበትን ልምዳቸውን ለዛሬዎቹ ተተኪ ወጣት መሪዎች የሚያካፍሉበት የመማማሪያ መድረክ ነው:: በመጀመርያው ዙር የስራ አስፈጻሚዎች መድረክ የአዲስ ቻምበር ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ በዚህ መሰረት የአዲስ ቻምበር ፕሬዝደንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ የመሪነት ሚና ለአንድ ተቋም ውድቀትም ይሁን ስኬት ትልቁን ድርሻ ይይዛል በማለት ተናግረዋል::

አክለውም የንግድ ምክር ቤቱ ፕረዚደንት መድረኩ ወጣት የቢዝነስ ሥራ መሪዎችን አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል:: መድረኩ አባት እና እናት መሪዎች ፈተናዎችን በየጊዜው እየተጋፈጡ እንዴት በብልሃት አልፈው የሚመሩትን የቢዝነስ ተቋም ከውድቀት ወደ ስኬት እንዳሻገሩ በአካል ተገኝተው ለትውልድ የሚያስተላልፉበት ነው ብለዋል::

የንግድ ም/ቤቱ ዋና ጸሐፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር ሰፊ ዕውቀት እና የመሪነት ልምድ ባለቤቶች በጡረታ ከተገለሉ በኋላ በቤታቸው የሚውሉ እንጂ ያካበቱትን ሃብት ለትውልድ የሚያስተላልፉበት ባሕል በአገራችን የለም በማለት ባደረጉት ንግግር ገልጸዋል:: ዋና ጸሀፊው አክለውም እንዳሉት አዲስ ቻምበር በቢዝነስ መሪነት የካበተ ልምድ ያላቸው ዜጎችን በዚህ መድረክ እያቀረበ እወቀት ለማሸጋገር የሚያስችል ስራ መጀመሩን በመግለጽ በተለይ ወጣት መሪዎች ይህን ወሳኝ የሆነ መድረክ እንዲጠቀሙበትና የአመራር ጥበብና ልምድን እንዲቀስሙ ጥሪ አቅርበዋል::

በማስጀመሪያ ሁነቱ ላይ የተጋበዙት ዶ/ር አረጋ ይርዳው ቀርበው ከወጣትነት እስከ ወቅታዊ የስራ ተሞክሮአቸውን በስፋት አካፍለዋል:: ዶ/ር አረጋ ይርዳው የቀድሞው የሚድሮ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈጻሚ እና በአሁኑ ወቅት የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ሲሆኑ የበርካታ አመት የአመራር ልምድና ተሞክሮ እንዳላቸው በመድረኩ ላይ ተገልጿል::

በዚህ መድረክ ላይ ልምድና ተሞክርአቸውን ያካፈሉት ዶ/ር አረጋ ከ6ሺ በላይ ሰራተኞች ያሉትን ግዙፉን የሚድሮክ ኩባንያ በዋና ሥራ አስፈጻሚነት ለመምራት ሲታጩ በቀጥታ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ስለሚድሮክ በቂ መረጃ በመሰብሰብ ጥናት ማድረጋቸውን ተናግረዋል::

አንድ የሥራ መሪ በስሩ የሚገኙትን ሁሉንም ሠራተኞች በእኩል አይን ማየት አለበት የሚሉት ዶ/ር አረጋ መሪነት ደጋግሞ ማሰብ እና በፍጥነት ውሳኔ መስጠት እንዲሁም አሳታፊ መሆንን ይጠይቃል ብለዋል:: በመሪነታቸው ወራት በርካታ ከውጪ እና ከውስጥ የሚነሱ ትችቶች እና ፈታኝ ሁኔታዎችን ጆሮ ባለመስጠት ወደ 26 የሚሆኑ እህት ኩባንያዎችን አስተባብረው ለአመታት በጥበብ መምራታቸውን ተናግረዋል::

ይኸው የመማማሪያ እና የልምድ ልውውጥ መድረክ በአዲስ ቻምበር እና በSAK በተባለ አማካሪ ድርጅት ትብብር በወር አንድ ጊዜ በጋራ የሚዘጋጅ መድረክ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል::

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የህንድ የንግድ ልኡካን ቡድን በኢትዮጵያ ከሚገኙ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ጋር በጋራ መስራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ መከሩ



**በስታፍ ሪፖርተር**

የግሎባል ህንድ ቢዝነስ ግሩፕ እና የህንድ ዓለም አቀፍ ንግድ ምክር ቤት ኢንዱስትሪ እና ግብርና አባላት በኢትዮጵያ ያለውን የቢዝነስ እድል ለመገንዘብ መምጣታቸውን ገልፀዋል:: በፋርማሲዩቲካል ፣ ከሶሞቲክስ ፣ ፕላስቲክ ምርት ፣ የግብርና ፣ማሽነሪ እና ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ የተሰማሩ 19 የህንድ ኩባንያዎች በተመሳሳይ ዘርፍ ላይ ከሚሰሩ ኢትዮጵያዊያን ነጋዴዎች ጋር በጋራ ሊሰሩ በሚችሉበት መንገድ መክረዋል ::

የአዲስ ቻምበር ምክትል ዋና ፀሀፊ አቶ ዘካሪያስ አሰፋ የንግድ ለንግድ ውይይቱ ሲጀመር ለልኡካኑ ባደረጉት ገለፃ ንግድ ምክር ቤታቸው አንጋፋና ጠንካራ ንግድ ምክር ቤት መሆኑን ገልፀው የንግድ ግንኙነቱ ወደ ተግባር እንዲለወጥ ተቋማቸው አበክሮ እንደሚሰራ ተናግረዋል::

አዲስ ቻምበር ያነጋገረቻቸው የህንድ የንግድ ልኡካን አባላት በበኩላቸው በኢትዮጵያ ያለውን የቢዝነስ እድል ለማየት እንዲሁም በኢትዮጵያ ያሉ ምርቶችን ወደ ህንድ ማስገባት እንዲሁም የህንድ ምርቶችን ለመላክ ያለውን እድል ለማየት መሆኑን ገልፀዋል::

ኢትዮጵያዊያን ነጋዴዎች በበኩላቸው በአካል ተገናኝቶ መነጋገሩ በኦንላይን እና በስልክ ከመነጋገር የበለጠ እምነት እንደሚያሳድር ገልፀዋል::

አዲስ ቻምበር 17 ሺ አባላት ያሉት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ300በላይ የሚሆኑት የውጭ አገር ኩባንያዎች መሆናቸውን በውይይቱ ላይ ለማወቅ ተችሏል ::

# 26ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒት በጨረፍታ

**በስታፍ ሪፖርተር**

የንግድ ማስፋፊያ እና የማስታወቂያ ሥራ የዘመናዊ ንግድ ሥራ አመራር ቋሚዎች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው ይላሉ የንግድ ሥራ አዋቂዎች:: የንግድ ማስታወቂያ እና ማስፋፊያ ዘዴዎች መካከል አንዱ የንግድ ትርዒት ነው:: የንግድ ትርዒቶች ከአካባቢ እስከ ዓለም ማቀፍ ደረጃ ሊዘጋጁ ይችላሉ:: የንግድ ትርዒቶች አምራቹ ፤ ነጋዴው እንዲሁም ሸማቾች በአንድ ጣሪያ ሥር በማሰባሰብ አንዱ ከሌላው የሚገበያይበት፤ ቀጣይ የቢዝነስ ግንኙነት የሚመሠረትበት፤ እልፍ ሲልም የሽርክና ቢዝነሶች የሚጀመሩት፤ገዢና ሻጭ በተረጋጋ ሁኔታ ስለሚፈልጉት ምርቶች እና አገልግሎቶች በአካል ተገኝተው ፤በዓይናቸው አይተው እና በእጃቸው ዳስሰው በቂ መረጃ የሚያገኙበት አውድ ነው ማለት ይቻላል::

በአገራችን የተለያዩ የንግድ ማስፋፊያ ሁነቶች ይዘጋጃሉ:: ነገር ግን በአገራችን የመጀመሪያው የንግድ ትርዓት ፋና ወጊው አዲስ ቻምበር ላለፉት ሶስት አሥርት-አመታት መደበኛ የሆኑ 4 ዓለማቀፍ የንግድ ትርዒቶችን ሲያካሂድ ቆይቷል:: እነዚህ የንግድ ትርኢቶች በግብርና ፤ በህክምና ፤ በማምረቻው ዘርፍ ላይ ትኩረታቸውን ያደረገ አለምአቀፍ አውደርዮች ናቸው:: የዚህ አንዱ አካል የሆነውና በ2016 አ.ም ለሁለተኛ ጊዜ የተካሄደው የምክር ቤቱ የንግድ ትርኢት ከየካቲት 14 እስከ 18 2016 አ.ም በአዲስ አበባ ኢግዚቢሽንና ገበያ ልማት ማእከል ተካሄዷል::

በዚህ ዝግጅት ላይ የሁሉም የንግድ ዘርፍ ነጋዴዎች ማለትም አምራቾች፤ አቅራቢዎች፤ አቀናባሪዎች፤ አገልግሎት ሰጪዎች፤ጅምላ አከፋፋዮች፤ ፤ላኪዎች እና አስመጪዎች የተሳተፉበት አለምአቀፍ ንግድ ትርዒት ተካሂዷል:: ከፍተኛ የመንግሥት ሃላፊዎች፤አምባሳደሮች የኩባንያ ወኪሎች እና የትርዒቱ ተሳታፊዎች በተገኙበት የቢዝነስ ሁነት ላይ የአዲስ ቻምበር ፕሬዝደንት እና የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ተወካይ ንግግር አድርገዋል:: **“ይህ ዛሬ ያዘጋጀነው ሁሉን የንግድ ዘርፍ የሚያካትተው ዓለማቀፍ የንግድ ትርዒት በንግድ ሥራ ዘርፍ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የፈጠራ ክህሎት የንግዱሕብረተሰብ ትኩረት ሰጥተ ፈጠራን እንደባሕል እንዲይዘው የሚያስታውስ ነው። ንግድ በአዳዲስ ፈጠራ ካልታጀበ ፈጣን ዕድገት ፤ጥራት፤የደንበኞች እርካታ …የመሳሰሉ የተወዳዳሪነት ምልክቶች ሊኖሩ አይችሉም። ፈጠራ በባሕሪው ቀጣይ እና ሁሌም የማያቆም”** በማለት የአዲስ ቻምበር ፕረዚደንት መሰንበት ሸንቁጤ በመክፈቻ ንግግራቸው ወቅት ተናግረዋል::

“ፈጠራ ወይም ኢኖቬሽን ንግድና ኢንቨስትመንትን በማፋጠን ለአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ መንግሥት ኢኖቬሽን የበለጠ እንዲስፋፋ አስከዛሬ ካደረገው ጥረት በላይ መሄድ አለበት:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ለቴክኖሎጂ እና ለተስማሚነት ምዘና የንግዱ ሕብረተሰብ የሚጠየቀው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ መንግሥት ይህንን ተመልክቶ ማሻሻያ እንዲያደርግ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አናስተላልፋለን” በማለት የንግድ ምክር ቤቱ ፕረዚደንት አክለው ተናግረዋል::

በአለምአቀፉ የአዲስ ቻምበር የንግድ ትርኢት ላይ ንግግር ያደረጉት ሌላው ተናጋሪ የአዲስ በአበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ተወካይ አቶ መከተ አዳፍሬ ሲሆኑ **“መንግሥት ፈጣን ኢኮኖዊያዊ እድገት እና ወደ ኢንዱስትሪ ሽግግር በማድረግ አገራችንን ወደ መካከለኛ ገቢ አገራት ተርታ ለማስገባት ጥረት እያደረገ ነው** በማለት ተናግረዋል:: ነገር ግን አሁንም ያልተፈቱ ችግሮች እንዳሉ መንግሥት ይገነዘባል ያሉ ሲሆን የሎጂስቲክ እና የመጓጓዣ ወጪ ከፍተኛ መሆን፤ ከውጪ የሚገቡ የማንዩፋክቸሪንግ ግብዓቶች፤ በወጪ ንግድ ማበረታቻ ፖሊሲዎች ላይ ተከታታይ ጥናት እና ክለሳ አለመደረግ ፤ የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ፤ ዓለማቀፉን መመዘኛዎች ጥራት እና ደረጃ አሟልቶ ለውጪ ገበያ ማቅረብ አለመቻል፤ በገጠሩ በቂ የመሠረተ ልማት አለመኖር ንግድና የማምረቻ ዘርፉን በበቂ ሁኔታ እንዳያድግ የሚያደርጉ ማነቆዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው በማለት ጠቅሰዋል:: ሆኖም መንግሥት በተቻለ አቅም መሠረተ ልማቶችን እየገነባ ነው፤የአይሲቲ አገልግሎቶች ተደራሽ እንዲሆን እያስፋፋ እና የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን በመከለስ ላይ ይገኛል በማለት አክለው ተናግረዋል::\

በንግድ ትርዒቱ ላይ ከሁሉም የንግድ ዘርፎች እና አገልግሎቶች ለዕይታ ቀርበው ነበር::አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፤ በአገር ውስጥ የተሰናዱ ተተኪ ምርቶች፤ አልባሳት፤የግብርና ውጤቶች፤የፋይናንስ ተቋማት እና የፕላስቲክ አምራቾች እና የኤሌክትሮ መካኒክ አምራቾች ከተሳታፊዎች መካከል ይገኙበታል:: አኛም እየተዘዋወርን አንዳንዶቹን አነጋግረን ይዘው ስለቀረቡት ምርቶች እና አገልግሎቶች እንዲሁም አጠቃላይ ስሜታቸውን እና አስተያየታቸውን ሰጥተውናል:: ከነዚህ አስተያየቶች መካል የኤልክትሪክ ምርት ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች ይገኙበታል:: ኢሳያስ ታፈሰ ከኤል አውቶ ኩባንያ ኀሳባቸውን የሰጡ ሲሆን ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁን ሰዓት መኪና የቅንጦት ዕቃ ሳይሆን መሰረታዊ ፍላጎት ውስጥ እንደሚመደብ ተናግረዋል:: የኤሌክተሪክ መኪኖች በዚህ ሁለት ወር ውስጥ ብቻ 600 ደንበኞቻችንን ለመረከብ እየጠበቁ ናቸው ያሉ ሲሆን እንዲህ አይነት የንግድ ትርኢቶች ምርቶችን በማስተዋወቅና የገበያ እድል በመፍጠር አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ በማለት ለአዲስ ቻምበር ድምጽ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል::

**ሌላው የንግድ ትርኢት ተሳታፊ አሕመድ ጣሂር ጋሙር ሲሆን አህመድ ከሶማሊላንድ የፕላስቲክ ምርቶችን ይዞ ቀርባል።** “እኛ በፕላስቲክ ዘርፍ ላይ ለረዥም አመታት ተሰማርተን እንገኛለን:: በኢትዮጵያ የሚካዱት የ ኮንስትራክሽን እና ሰፋፊ የመስኖ እረሻዎች እንዳሉ እንሰማለን:: ዛሬ ከመጣን ጀምሮ በርካታ ጎብኚዎች ጋር ንግኙነተ ጀምረናል:: ስለምርቶቻችን መረጃ ስንሰጥ ቆይተናል:: ደስ የሚል እንቅስቃሴ እየደረግን ነው:: የዘን የቀረብነው የፕላስቲክ ምርቶች ጥራት እንዳላቸው ጎብኚዎች ነግረውናል:: ኩባንያቸን የጋሙር ፕላስቲክ ኢንዱስትሪ በድሬዳዋ እና በጀግጅጋ ከተሞች ቅርንጫፍ ቢሮዎችን ለመክፈት ዕቅድ አለው” በማለት ለአዲስ ቻምበር ድምጽ ተናግረዋል::

ሌላው የ26ኛው አለምአቀፍ ንግድ ትርኢት ተካፋይ የሆነው አንኩር ቺትሮዳ ከህንድ ሲሆን የጎያም ኩባንያ በመወከል አዲስ አበባ ተገኝታል:: **“እኛ የመጣነው ከሕንድ ነው። ድርጅታችን የሚያመርታቸውን የተለያዩ ማሽሪዎችን ይዘን መጥተናል። ዛሬ ይዘን የመጣናቸው መሽነሪዎችመካከል የምግብ ዘይት መጭመቂያ እና ማቀነባበሪያ ማሽኖች በብዛት ይገኙበታል። በኢትዮጵያ ያለውን የምግብ ዘይት ፍላጎት ከፍተኛ መሆኖኑን እናውቃለን። የጎሮ መኖ ማቀናበሪያ ማሽኖችም አሉ”** በማለት ለአዲስ ቻምበር ድምጽ ኃሳቡን አካፍሏል::

ጎያም ጄይን የጎያም ኩባንያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በ26ኛው አለምአቀፍ የንግድ ትርኢት ላይ በመሳተፍ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ አዲስ አበባ ይዘው በመምጣት የገበያ እድሎችን ለማፈላለግ አስበዋል::

**“እኔ ለገበያ ጥናት ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ አንድ ነገር ለመታዘብ ችያለሁ። ይኸውም የቅባት ዕህሎችን ታመርታላችሁ። ያጥሩ ነገር ነው። ነገር ግን የምግብ ዘይት ከውጪ ደገሞ ትገዛላችሁ። እግዲህ እዚህ ላይ አንድ ነገር እንዳስብ አደረገኝ ። ይኸውም የምግብ ዘይት መጭመቂያ በማምጣት የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት እየሞከርን ነው። የኛ የምግብ ዘይት መጭመቂያ ማሽኖች በቤተሰብ ደረጃ የሚያገለግሉትን ጨምሮ እስከ ሜጋ መጭመቂያ ማሽኖችን በሊዝ ፋይናንሲንግ አማካኝነት እያቀረብን ነው ፡አዲስ ቻምበርን እናመሰግናለን”** በማለት ኃሳባቸውን አካፍለዋል::

# አዲስ ቻምበር “የሥራ መሪዎች መድረክ” አገልግሎትን በይፋ ጀመረ



ከ ገጽ 4 የዞረ

አዲስ ቻምበር በቅርቡ በጀመረው “የሥራ መሪዎች መድረክ ” ዝግጅት ላይ ተገኝተው ለረዥም አመታት በኩባንያ መሪነት ያካበቱትን የረዥም ጊዜ ልምድ፤ ያጋጠሙዋቸው ፈተናዎች፤ ፈተናዎችን በጥበብ አልፈው ለስኬት ካበቋቸው ብልሃቶች፤ እንዲሁም የዘመናዊ የመሪነት ፍልስፍና እና መሠረታውያን፤ ለበርካታ ወጣት የኩባንያ መሪዎች እና ለታዳሚዎች ካካፈሉዋቸው ቁምነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

ዶ/ር አረጋ ሲጀምሩ 5 የነበሩትን ኩባንያዎች በማሳደግ ሌሎች 20 አዳዲስ ኩባንያዎችን አስፋፍተው በጠቅላላ 26 የቢዝነስ ድርጅቶችን ለስኬት ያበቁ አንቱ የተባሉ በሳል የቢዝነስ የሥራ መሪ ናቸው ፡፡

እርሳቸውም አዲስ ቻምበር በየወሩ በሚያዘጋጀው “የሥራ መሪዎች መድረክ” ላይ ተገኝተው ያካበቱትን የአመራር ጥበብ እና ዕውቀት ሁሉ ሳይሰስቱ ለዛሬዎቹ አመራሮች እና ወጣት የቢዝነስ መሪዎች እንካችሁ ብለዋል፡፡

እኛም ከብዙ በጥቂቱ ጠቃሚ ናቸው ያልናቸውን ነጥቦች አሰባስበን እና አሳጥረን ያዘጋጀነውን እነሆ፤

አንድ የሥራ መሪ የራሱ ይሆነ የአመራር ‘Authentique’ ስልት መከተል አለበት፡፡ የሚመራውን ድርጅት አጥንቶ ጠንቅቆ ማወቅ አለበት፡፡ እንጂ ለመሞከር ያህል በሚል የአመራር ዘይቤው ከሌሎች የተቀዳ መሆን የለበትም፤

በዓለም ላይ አንድ እና ወጥ የሆነ የአመራር ስልት ወይም መርሕ የለም፡፡ ስለዚህ አንድ የቢዝነስ መሪ በዙሪያ እንዳለው ተጨባጭ ሁኔታ፤እንደ አገሩ፤አካባቢው ፤ እንደ ባሕሉ አገናዝቦ መምራት መቻል ያስፈልጋል፤

አንድ የሥራ መሪ ትልቁን ትኩረት መስጠት ያለበት የድርጅቱን ንብረት ወይም ቁሳቁስ ሳይሆን አስቀድሞ ሰውን መሆን አለበት ፡፡ የመሪው ትኩረት ሠራተኞቹ ላይ መሆን አለበት፤

አንድ የኩባንያ መሪ የሰራተኛ ማሕበራትን ከመራቅ ይልቅ ማቅረብ ፤ ማጠናከር፤ ከማሕበሩ ጋር ጥሩ ግንኙነት መመሥረት፤ማሕበሩን የመፍትሔ አካል ማድረግ አለበት፤

የኩባንያ/ የቢዝነስ መሪዎች በሕብረተሰቡ ዘንድ ስለሚመሩት ድርጅት አንድ አይነት እና ወጥ የሆነ ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል፤

አንድ የኩባንያ መሪ የሚመራውን ኤንተርፕራይዝ/ዞች (Core Function) ዐቢይ ተግባር /ሥራ አስቀድሞ በደንብ መገንዝብ አለበት፡፡ ይንን ያወቀ መሪ ፖሊሲ በማውጣት የድርጅቱን ዓላማ በሥሩ ያለውን የሰው ኃይል አስተባብሮ ማሳካት ይችላል፤

የበታች የሥራ ክፍል ኃላፊዎችን ማሰልጠን፤አቅም ማሳደግ እና ማብቃት ተተኪ መሪዎችን ማፍራት ከዘመናዊ የኩባንያ መሪዎች ይጠበቃል፤

አንድ የኩባንያ መሪ ከትርፍ ስኬት በተጨማሪ ለሌሎች (ለሠራተኞች ፤ ለአካባቢው ሕብረተሰብ) መኖርን ማሰብ አለበት፡፡ ሠራተኞችን ከመክሰስ ይልቅ፤ ቀርቦ መጠየቅ እና ችግሮቻቸውን በጥምና አዳምጦ መፍትሔ መስጠት አለበት፡፡ / A Life Living For Others is the Life Worth Leaving/ ከአልበርት አየንሽታይንን አባባል በማስታወስ፡፡

# የሴቶች የአመራር አቅምን ማሳደግ የሚያስችል ስልጠና ተሰጠ

**ሴቶች ወደ አመራርነት እንዲመጡ በተቋማት ውስጥ ምቹ ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚገባ ተጠቅሷል።**

**በሰናይት እሸቱ**





የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ተቋም ያዘጋጀው ስልጠና በተለያዩ ተቋማት ውስጥ የአመራርነት ልምድ ባላቸው በወ/ሮ ሂክመት አብደላ እና በሌሎች ባለሞያዎች ተሰጥቷል፡፡

ስልጠናውን በተለያዩ ተቋማት በአመራርነት እንዲሁም በቦርድ ውስጥ የመስራት እድሉን ያገኙ ሴቶች ተሳትፈውበታል፡፡

በአመራርነት ቦታ ያሉ ሴቶች የሚገጥሟቸው ችግሮች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጥሩት ተጽኖ እንዲሁም ጾታ ተኮር ፍረጃ ላይ ያተኮሩ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡

በአመራርም ሆነ በሌሎች ስራዎች ላይ ያሉ ሴቶች ስራዎቻቸው ላይ በማተኮር ወደ አመራርነት እንዳይደርሱ ተቋማት የሚሞክሩበትን እድል የማይሰጡ እና በስልጠና እና በትምህርት ሊሞሉ የሚችሉ ክፍተቶችን በቀጥታ ከጾታ ጋር በማያያዝ ወደኋላ የሚያስቀሩ አሰራሮችን ሲከተሉ የቆዩ መሆናቸው ለሴቶች ወደ አመራርነት መምጣት እንቅፋት እንደነበሩ ወ/ሮ መሊካ በድር የዘምዘም ባንክ ዋና ስራ አስኪያጅ ልምዳቸውን ባካፈሉበት ወቅት ገልጸዋል፡፡


የምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ተቋም የአመራሮችን አቅም ለማጎልበት የሚያግዙ ተከታታይ ስልጠናዎችን የሚሰጥ ሲሆን የሴቶችን የአመራር አቅም ለማጎልበት የሚሰጡ ስልጠናዎች ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው ተብሏል፡፡

በምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ተቋም በተዘጋጀው ስልጠና ሴቶች የአመራርነት አቅማቸውን ማሳደግ እንዲችሉ የሚረዱ የልምድ ልውውጦች፡የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን እንዲሁም አመራርነትን እና ሌሎች ሃላፊነቶችን አመጣጥኖ መሄድ የሚችሉበትን መንገድ የሚጠቁሙ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡

በስልጠናው ንግድ ምክር ቤቱ እንደሃገር ያለውን ክፍተት በመረዳት የዳይሬክተሮች ተቋምን ማቋቋሙ ወሳኝ መሆኑን ያነሱት ወ/ሮ ሂክመት ከቦርድ ጋር የተያያዙ የአመራር ክህሎቶችን ለማዳበር እንደሚያግዝ ገልጸዋል፡፡

በምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ተቋምም የሴቶችን የአመራር አቅም የሚገነቡ ስልጠናዎች በቀጣይ እንደሚካሄዱ ታውቋል፡፡

# ፒፒፒ... የግሉ እና የመንግሥት ትብብር ለፈጣን እድገት




**በከፍያለው ዋሲሁን**

Private Public Partnership ወይም በእንግሊዝኛው ምዕጻሩ -PPP ከቅርብ አሥርተ አመታት ወዲህ በፅንሰ ሃሳብና በተግባር እየተለመደ የመጣ የቢዝነስ እና የልማት ሞዴል ነው:: ትውልዱ በ13ኛ ው ክዘመን በአውሮጳ ሲሆን ዛሬ ላይ አንድ የቢዝነስና የልማት ሞዴል ሆኖ ያገለግላል:: እስከ አሁን በአማርኛ አቻ ትርጉም ያልተሰጠው ፐብሊክ ፓርትነርሺፕ እንደየቦታው የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ትብብር፤የነጋዴውና የመንግሥት ሽርክና፤ የግሉ ዘርፍ እና የመንግሥት ሽርክና፤የሕዝብና የግል ትብብር ወዘተ እየተባለ ጥቅም ላይ ይውላል:: ለዚህ ዝግጅት ሲባል የመንግሥትና የግል ሽርክና እያልን እንጠቀምበትና የመንሥትና የግል ሽርክና በተግባር ምን እንደሚመስል አንዳንድ ምሳሌዎችን እናንሳ:: በአውሮጳ እና በሰሜን አሜሪካ አገራት ይህን አይነት ሽርክና/ትብብር የሚታየው በብዛት በትላልቅ የሆኑ ብዙ ሃብት እና ቴክኖሎጂ የሚጠይቁ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ነው::

ለምሳሌ የኃይል መመንጫዎች፤ የማዕድናት እና የከርሠምድር ሃብቶች ጥቅም ላይ በሚያውሉ የልማት ፕሮጀክቶች፤ በሰፋፊ እርሻዎች፤የጠፈር ምርምር ፕሮጀክቶች መሰል የግልና የመንግሥት ሽርክናዎች ይታያሉ:: በፒፒፒ የመንግሥት ሚና በአብዛኛው ነግዶ ለማትረፍ ሳይሆን በትብብሩ ሂደት የሥራ ዕድል መፍጠር እና ኢኮኖሚውን ማንቀሳቀስ ሲሆን የግሉ ዘርፍ ደግሞ ባለው የፋይናንስ ፤በዕውቀት እና በቴክኖሎጂ ድጋፍ በማድግ ይሆናል::

የዛሬው ጽሁፍ የዚሁ የፒፒፒ ወይም የግል እና የመንግሥት ሽርክና በተግባር የታየበት እና እስካሁን ባለው ሂደትም ውጤት ማስመዝገብ ስለጀመረ አንድ ፕሮጅክት ላየ ያተኩራል::

ፋብሪካው ብሉኮ ቴክስታይል አክሲዮን ማሕበር ይባላል ቀደም ሲል አይካ አዲስ በሚል ስም በቱርክ ባለሃብቶች ይዞታ የነበረ እና ስመ ጥር አልባሳት እያመረተ ለውጪ ገበያ የሚልክ ግዙፍ ፋብሪካ ነው:: ኩባንያው በተለያዩ ምክንያቶች ምርት አቁሞ እና ወደ 4 አመታት ያህል ተዘግቶ እንደነበር መረጃዎች ነግረውናል:: የአሁኑ የፋብሪካው መሪዎች ይህንን ሰፊ የአገር ሃብት የፈሰሰበትን ፋብሪካ መልሶ ለማስነሳት የተለያዩ አማራጮች ተሞክረው ሊሳኩ አልቻሉም ነበር:: ለአመታት ተዘግቶ ሠራተኞችን በትኖ እና አፍራሽ የኢኮኖሚ ኪሣራ አስከትሎ በመጨረሻም ከሞቶ የተቀበረ ፋብሪካ አንዴት ነፍስ ዘርቶ ዛሬ ማየት ተቻለ ብለን ስንጠይቅ ያገኘነው መልስ በግል ባለሃብቶች እና የመንግሥትን ጥረት በማስተባበር አንድ ለአገር የሚበጅ ሥራ መሥራቱን ነበር::

የመንግሥት ዘርፍ ግን የፖለቲካውን ፤ የሕግ አውጭውን እና የቁጥጥር ማዕቀፉን፤የፖሊሲ ድጋፍ ማድረግ፤ የፕሮጀክት ዝግጅት እና የቁጥጥር ሥራዎችን በማከናወን እና የህዝቡን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ወሳኝ ሚና እንደተጫወተ ሰምተናል :: ዛሬ ላይ ይኸው ፋብሪካ ወደ 3ሺህ ለሚሆኑ ወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጥሯል:: በ20 ሄታር ላይ የገነባው ፋብሪካ በምሥራቅ አፍሪቃ ትልቁ የጨርቃጨርቅ እና የአልባሳት ማምረቻ የነበረ ሲሆን አሁን ላይ ዕድሳት እና ጥገና ተደርጎለት በ60በመቶ አቅሙ እየተንቀሳቀሰ ነው ተብሏል:: በግል ባለሃብቶች እና በመንግሥት ትብብር ትንሣኤውን ያገኘው ማምረቻ ቀስ በቀስ ወደ ገበያ እየገባ እና ራሱን መደጎም የጀመረ ይመስላል::

የመንግስት-የግል ሽርክና ዓይነቶች አንደኛ በመንግስት እና በባለሃብቶች መካከል እርስ በርስ የሚስማሙ ማንኛውም አይነት መስተጋብር ሲሆን 2ኛው የገንዘብ ኪራይ ( ማከራየት); 3ኛው ደግም እንደህ አይነት የመንግስት-የግል ድርጅቶች ላይ የመሰራ ትብብር ናቸው::

ይህን መሰል የግል ባለሃብቶች እና በመንግሥት ሽርክና የሚገነቡ አልያም ከሥረው ከኪሣራ የሚያገግምበት አሰራር በአባዛኛው ግዜ ቀጣይነት የላቸው የልማት ፕሮጀክቶች ሆነው እናገኛቸዋል:: ለማሳሌ በዓለም ከሚገኙት 3,000 ሺህ የንግድ አየር ማረፊያዎች ውስጥ 19 በመቶው ፒፒፒዎች ሲሆኑ ከጠቅላላው ተሳፋሪዎች ውስጥ 30 በመቶውን ይይዛሉ::

አንድ መደበኛ PPP ለመንግስትም ሆነ ለግል ዘርፎች በርካታ ጥቅሞችን ሊያቀርብ ይችላል :: መንግስታት የተጠናከረ በጀትን የሚጋፈጡ እንደመሆናቸው መጠን የመንግስት የልማት ግጭቶች (PPPs) የግል ፋይናንስን የማግኘት እና የመንግሥት ወጪዎች በተዘረጉበት ወቅት የካፒታል ገበያዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል መንገድ ይሰጣሉ :: በተገቢው ሁኔታ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ትርፋማነትን ፣ አያያዝን እና አሰራሮችን ለማሻሻል ፣ የፈጠራ ስራዎችን እና የአሠራር ብቃቶችን ለማስተዋወቅ እና አጠቃላይ የአገልግሎት ደረጃዎችን ለማጎልበት ይረዳል::እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ከትብብሩ የሚመነጩ ክህሎቶች እና ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽነት ለማሳደግ ፣ ለተሻሻለ ብቃት እና አፈፃፀም የበለጠ ማበረታቻዎችን በመስጠት መንግሥት የታደጋቸውን ተቋማት ወደ ልማት በመቀየር ያሳየው ውጤት ይበል የሚያሰኝ ሲሆን በሌሎችም ተቋማት በመድገም የግሉና የመንግሥት የትብብር ባሕልን ማስፋፋት ይገባል እንላለን::

## አዲስ ቻምበር ከኢትዮጵያ ቡና ማሕበር ጋር የመግባቢያ ሠነድ ተፈራረመ

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

በሁለቱ ወገኖች በኩል በተፈረመው ሠነድ መሠረት ንግድ ምክር ቤቱ በአድቮኬሲ፤በጥናት እና ምርምር እንዲሁም በስልጠና ለማሕበሩ ድጋፍ እንደሚያደርግ ተገልጿል:: በስነ-ሥርዓቱ ላይ የአዲስ ቻምበር ፕሬዝደንት ወ/ሮ መሠንበት ሽንቁጤ አዲስ ቻምበር የዓለም ንግድ ም/ቤት አባል እንደመሆኑ መጠን ከተለያዩ ባለድርሻዎች ጋር በመነጋገር በአሁኑ ወቅት በቡና የወጪ ንግድ ላይ የተከሰተውን ችግር ለመቅረፍ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል ብለዋል::

የኢትዮጵያ ቡና ማሕበር ፕሬዝደንት አቶ ደሳለኝ ጀማ በበኩላቸው ማሕበራቸው ከአንጋፋው ንግድ ም/ቤት ጋር በጋራ መሥራት በመቻሉ ደስታ ይሰማዋል ብለዋል:: ንግድ ም/ቤቱ እና ማሕበሩ የግሉ ዘርፍ አካል በመሆናቸው እና በአገራችን ኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ሚና ያላቸው እንዲሁም ተዛማጅ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ናቸው:: ስለዚህ የስምምነቱ ሠነድ ሁለቱም ወገኖች እየተናበቡ ተመጋጋቢ ሥራዎችን ለማከናወን ያስችላቸዋል ብለዋል::

ቀደም ሲል ማሕበሩ በቡና ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ባለድርሻዎች የተሳተፉበት የውይይት መድረክ በየመን የሚንቀሳቀሱት የሁቲ ታጣቂዎች በመርከቦች ላይ በሚሰነዝሩት ጥቃት ሳቢያ በቀይ ባሕር ንግድ መስመር ላይ ውጥረት መንገሱ ተወስቷል:: በተፈጠረው የንግድ ስጋት ሳቢያ ዋና ዋና የጭነት መርከብ ኩባንያዎች ወደ ጂቡቲ ወደብ የሚያደርጉትን ጉዞ ማስተጓጎሉ ተነግሯል:: የችግሩን መላ ለማፈላለግ አንድ ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋሙን እና ኮሚቴውም በቅርቡ ለመንግስት የውሳኔ ሃሳብ አንደሚያቀርብ የማሕበሩ ባለሥልጣናት ገልጸዋል::




አዲስ ቻምበር

ADDIS CHAMBER

Addis Chamber Training Institute (ACTI)

## List of Upcoming Training Programs

| No. | Training Topic | Date | Time | Training Fee | | Venue | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | Member | Non-Member. | | |
| 1 | Records Management | March 25-29, 2024 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 2 | Advanced Customer Service | March 25-29, 2024 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 3 | Emotional Intelligence | March 26-27, 2024 | 8:30AM - 5:30PM | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 4 | Transformational Leadership | March 26-28, 2024 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 5 | Strategic Marketing Management | March 26-28, 2024 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days` |
| 6 | Taxation in Ethiopia | April 1-5, 2024 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 7 | Supervisory Management | April 1-5, 2024 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 8 | Change Management | April 2-3, 2024 | 8:30AM - 5:30PM | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 9 | Asset Valuation | April 8-19, 2024 | 8:30AM - 12:30PM | 6,383 | 7,659 | ACTI | 10 half days |
| 10 | Marketing Research | April 8-12, 2024 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 11 | Decision Making and Problem Solving | April 15-19, 2024 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 12 | Training of Trainers | April 16-18, 2024 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 13 | Effective Report Writing & Presentation Skills | April 22-26, 2024 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 14 | International Trade Service & Ethiopian Export/Import Practice | April 22-26, 2024 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |

**For further information, please contact the Training Institute through 011-551-3882, 0911194965, 0913249766, 0911343078, 0911160585, dejedesalegn@gmail.com, assefakasa2@gmail.com, hiwottlhn9@gmail.com and hime.by@gmail.com.**

# የምጣኔ ሀብታችን ለዉጭ የገንዘብ ተቋማት ክፍት መሆኑ አንድምታ




**እጹብድንቅ ስለሺ (ዶ/ር)**

በስነ ምጣኔ ሀብት ትምህርት አንድ ወሳኝ ነጥብ አለ። እሱም "ከእያንዳንዱ ምርጫህ ጀርባ ፣ ሌላ የተሰዋ ጥሩ አማራጭ አለ" የሚል ነው ወይም -Opportunity Cost የምንለው። የትኛዉም ስለሚጠቅም ነገር የሚደረግ የግለስብም ይሁን የድርጅት ወይም አገራዊ ዉሳኔ ሁልጊዜ ይዞት የሚመጣ ተጓዳኝ የሚከፈል ዋጋ አለው። እንደ ምሳሌ አንድ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጊዜውን ትምህርት ላይ ለማሳለፍ ሲወስን ለትምህርት ገንዘብ ከማዉጣቱ በተጨማሪ፣ ጊዜዉን በሌላ ሥራ(የትምህርት ዓይነት) ላይ አዉሎት ቢሆን ኑሮ የሚያገኘዉን ገቢና የሚያፈራዉን ሀብት ያጣል። በሥራ የተሠማራዉ በፈንታዉ ሊያካብት የሚችለው መደበኛ እዉቀት ያልፈዋል። የሰዉ ልጅ እንደ ግል ፣ አገር እንደ ማህበር የጊዜ ዉሱንነትና የሀብት እጥረት አለባቸዉና ባንድ ጊዜና በጥቂት ሀብት ብዙ ተግባር ለማከናወን ስለማይቻል ሁልጊዜ ዉሳኔዎች በሌሎች አማራጮቹ መስዋእትነት የሚቆሙ ናቸው። ይህን ጉዳይ ማንሳቴ በቅርቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቀባይነት ያገኘው የዉጭ ባንኮች እንዲገቡ የሚፈቅደው ረቂቅ ጋር ተያይዞ ሀሳቦች እዚህም እዚያም ሲነሱ በማየቴና በመስማቴ ነው። የዉጭ ባንኮች የሚኖራቸው የባለቤትነት ድርሻ እና የሚሰጧቸው የአገልግሎት ዓይነቶች ዉስንእንደሆኑ የረቂቁን ዝርዝር ጽሁፍ ያዩ ሰዎች ጽፈዋል።ያም ሆነ ይህ በግዜ ሂደት የኢትዮጵያ ገበያ ሳቢ ሲሆን፣ያገር ዉስጥ ባንኮች በልበ ሙሉነት ለመወዳደር ሲበቁ፣ የአክስዮን እና የዉጭ ምንዛሪ ገብያው ሲዳብር፣ ገንዘባዊው ክፍለ ምጣኔሀብት በደንብ መከፈቱ አይቀርምና ከዚህ ጋር ተያይዞ ያሉትን አተያዮች፣ ሙግቶችና፣ ተሞክሮዎች ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

ለመሆኑ የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ለዉጭ የገንዘብ ተቋማት ክፍት መሆኑ አንድምታዉ ምንድ ነው? የገንዘብ ዘርፉ ለዉጪው ዓለም ክፍት ይሁን ዝግ የሚለው የሚያከራክር ጉዳይ ሁኖ ይገኛል። ክርክሩ በፖሊሲ አርቃቂ እና አጽዳቂዎች እንዲሁም የልማት ሀሳብ አፍላቂዎችን የሚያካትት ነው። ጉዳዩ ባለፉት አርባ ዐመታት በተለይ በማደግ ላይ ባሉ አገራት የክርክር እና የውይይት አርዕስት ሁነው ከቆዩት ከአጠቃላይ የመንግሥት ምጣኔሀብታዊ ሚና ቅነሳ( economic liberalization) ድርጅቶችን ከመንግሥት ይዞታ ወደ ግል ማዘዋወር(privatization) እና የተንዛዛ እና ለግሉ ዘርፍ የሥራ እንቅስቃሴ መሰናክል የሚፈጥሩ ደንቦችን እና አሠራሮችን የመቀነስ እና የማሻሻል(deregulation) ሀሳቦች ጋር የተዛመደ ነው። እነዚህ እርምጃዎች በአንድ መልኩ ያገር ዉስጥ ባለሃብቶች ከመንግሥት ጫና መላቀቅና መንግሥትም እራሱ ህግ አዉጭ እና ራሱ የገበያ ተዋናይ እንዳይሆን የሚከለክሉ ሲሆኑ፣ በሌላ መልኩ ደግሞ ምርት እና አገልግሎት እንዲሁም ኢንቨስትመንት ያለብዙ መሰናክል ካገር ወዳገር እንዲንቀሳቀስ ለማስቻል የታሰቡ ናቸው። ይሁንና ባደጉ አገራት የሚገኙ ጠብደል ጠብደል ድርጅቶች ለብዙ አመታት ልምድ ያካበቱና ለመቆጣጠር በሚያስቸግር መልኩ(ግብር አከፋፈል፣ የፖለቲካ ተጽዕኖ...) ስለሚንቀሳቀሱ ፣ የድሃ አገራትን ምጣኔ ሀብት ለነዚህ ጠብደሎች መክፈት ተገቢ አይደለም የሚል ክርክር ሲቀርብ ቆይቷል። ይህ እንግዲህ ስለአጠቃላይ የምጣኔሀብት ዘርፉ ሲሆን ፣ በገንዘብ ነክ ተቋማት መግባት ወይም አለመግባት ላይ ያለዉ ሙግትም ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው።በዚህ ዙሪያ ያሉ አተያዮችን እንደሚከተለው በሦስት ፈርጅ አቀርባለሁ። እሊህም፣ ካልደፈረሰ አይጠራም፣ ጎመን በጤና እና ጎመን በሥጋ(ት) ይሆናሉ።

(ሀ) ካልደፈረሰ አይጠራም ፦ እነዚህ ጫፍ ረገጥ እና ወደ ሥርዓት አልበኝነት ማዕዘን የሚጠጉ ሲሆኑ፦ በፖለቲካ ዝንባሌያቸው የመንግሥትን ከግለስቦች ቀጠና መራቅ፣ በማህበራዊ ፍልስፍናቸው የግለሰብን ለማህበረሰባዊ ወግ ደንታ ቢስነት፣ በምጣኔሀብት አተያያቸው ምርትና አገልግሎት ድንበር ሳይገድባቸው፣ ማነቆ ሳይበዛባቸው ከቦታ ቦታ እንደልብ እንዲቀሳቀሱ የሚሹ ናቸው። አምራችና ሸማች ያለ መንግሥታዊ ሳንካ በፈቃዳቸው ቢገናኙ ህይወት ይሠምራል ባይ ናቸው። ከባንኮች መግባት አለመግባት ጋር የሚያያዝ አሳባቸው የሚቀዳዉ ከዚህ ነው። በነሱ አተያይ ነፃ ንግድ ብቸኛዉ የሀብትና የድሎት መንገድ ነው። በገበያ የሚከሰቱ የገንዘባዊ ክፍለ ኢኮኖሚ ቀዉሶች፣ የገበያ መናጋት እና አጠቃላይ ምጣኔሀብታዊ ምስቅልቅሎች ምንጫቸው የመንግሥታት ጣልቃ ገብነት እንጂ ገበያ ራሱ አይደለም ብለው ይከራከራሉ። በነፃ ገበያ ሥሪት በራሱ የሚፈጠሩ ቁስሎችና ህመሞች ግን በራሱ በገበያው አካል ዉስጥ ባሉ የበሽታ ተከላካይ ሃይላት(አቅርቦትና ፍላጎት) ታክመው ይድናሉ። የሚወስዱት ጊዜም አጭር በመሆኑ " የዉሻ ቁስል" ዓይነት ነው ባይ ናቸው። መንግሥት ጋዉኑን ለብሶ መድኃኒት ልዘዝ ቢል እንዳታምኑት ፣ የሚያዝዛቸው መድሃኒቶች ሁሉ ከበሽታዉ የባሰ ጉዳት የሚያስከትሉ ናቸው ይላሉ። በነሱ መነፅር፣ የዉጭ ባንኮች ሲገቡ ይህን ተከትሎ የሚመጡትን

(1) የገንዘብ ዘርፉ መደርጀት፣

(2) ብድርና ቁጠባ ስለሚስፋፋ ንግድ እንዲሳለጥ፣ ምርት እንዲበረክት ስለሚያደርጉ ያንድ አገር ምጣኔሀብት ያድጋል የሚል መሞገቻ ያቀርባሉ።

(3) በገንዘብ ተቋማት መካከል ውድድር ስለሚጠፍ አንድም ተገልጋዩ ይጠቀማል(ቆጣቢ ከፍተኛ ወለድ በማግኘት፣ ተበዳሪ ዝቅ ያለ ወለድ በመክፈል) አንድም ቀልጣፋ እና አትራፊ ያልሆኑ ባንኮች ከገበያዉ ገለል ስለሚሉ የሀብት ብክነት ይቀንሳል።

(4) ከባንኮች አንፃር ሲታይ ደሞ የተሻለ ትርፍ ወደሚያገኙበት አገር እንደልብ መንቀሳቀስና መወዳር ስለሚችሉ አትራፊነታቸዉን ይጨምርላቸዋል የሚል ሙግትም ይታከልበታል።

(5) የዉጭ ባለሀብቶች ሲገቡ የዉጭ ምንዛሪ ይዘው ስለሚመጡ ከዚህ በተጨማሪም ከነሱ ጋር ትስስር ወይም አመኔታ ያላቸው በአምራች ዘርፍም ይሁን በሌላ የአገልግሎት ዘርፍ ሊሠማሩ የሚችሉ ድርጅቶች አብረዋቸዉ ይተማሉና እድገት ይመጣል ብለዉ ይሞግታሉ። እንደዚህ አይነት አስተሳሰቦች የሚቀነቀኑት ቀድመው ሀብት በሰበሰቡ አገሮች ዉስጥ የሚነሱና የትም አገር ሂደን ብንወዳደር ወይም ሌላዉ እኛ ዘንድ ቢመጣ ማሸናፋችን አይቀሬ ነው ብለው የሚያምኑ ናቸው። ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያት ብዙም ተቀባይነት የላቸዉም ።

ከነሱ በትቃራኒ ደሞ የወ/ሮ ምጣኔሀብትን" ያዝ እጇን፣ዝጋ ደጇን" ብለው መንግሥትን የሚያማክሩ ምሁራን እና የፖሊሲ ሰዎች አሉ። እነዚህን "ጎመን በጤና" ልንላቸው እንችላለን።

(ለ)ጎመን በጤና፦በማደግ ላይ ባሉ አገራት ደሞ( መቼ ይሆን እድገታቸውን የሚጨርሱት?) ያጠቃላይ ምጣኔሀብቱን ቧ ብሎ መከፈት በተለይ ደሞ እንደ ባንክ ያሉ ተቋማትን ለዉጭ ባለሀብት መክፈትን ከፖለቲካ፣ ከፀጥታ፣ እና ከምጣኔሀብታዊ ሉዓላዊነት አግባብ እያዩ "አናስገባም የዉጭ ባንክ፣ እንዳንታወክ" ብለው ሲያንስ በመንግሥት ሥር ባሉ ባንኮች፣ ሲበዛ አገር በቀል በሆኑ የገንዝብ ተቋማት ሀይል ብቻ ምጣኔሀብቱን ማሳለጥ እንችላለን የሚሉ ይገኙበታል። ከሙግቶቻቸው መካከልም፣ ከዉጭ ባንኮች መግባት ጋር ተያይዞ

(1) የገንዘብ ነክ ቀውስ፣

(2) የምንዛሪ ገበያ ቀዉስ እና

(3)የገበያ አለመረጋጋትና የአጠቃላይ ምጣኔህብታዊ ምስቅልቅል በተደጋጋሚ ይከሰታል የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ።

(4)በተጭማሪም ከዉጭ የሚገቡ ባንኮች ብድር የሚያቀርቡት ከፍ ከፍ ላሉ እና ከዉጭ ዓለም ጋር ግንኙነት ያላቸው ወይም ምርታቸው በቀላሉ ከአገር አገር ሊንቀስቀስና እና ትርፍ ሊያመጣ የሚችሉት ላይ ሲሆን፣ ትናንሽ ድርጅቶች እና ምርታቸው ለዉጭ ንግድ ሊዉል የማይችል ድርጅቶች ከዉጭ የገንዘብ ተቋማት መግባት እምብዛም በቀጥታ አይጠቀሙም።

(5) ባለሙያዎችን ካገር ዉስጥ ባንኮች በማስኮብለል የሚያጋብሱት ትርፍ ዉጭ ላሉ ባለድርሻዎቻቸው ስለሚያከፋፍሉ የተማሩ ሰዎች

ላገራቸው "የቅርብ ሩቅ/ ያገር ዉስጥ ስደተኛ" እንዲሆኑም ያደርጋሉ:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ባለሙያ ፈልሶባቸው፣ ደንበኛ ቀርቶባቸው ከነጭራሹ የሚዘጉ ወይም በሌሎች ጠንካራ ባንኮች እቅፍ ዉስጥ የሚገቡ ያገር ዉስጥ ባንኮች አይጠፉም::(6) ምናባልባት ለጊዜው ሊጠቅም የሚችል የዉጭ ምንዛሪ ወደ ገበያዉ ቢያፈሱም፣ በጊዜ ሂደት ለባለ ድርሻዎቻቸው ትርፍ ማከፋፈል ሲፈልጉ የዉጭ ምንዛሪ ስለሚፈልጉ፣ የዶላር እጥረት እና የካፒታል ሽሽት የሚፈጥሩበት እድልም ይኖራል::

(ሐ)ጎመን በሥጋ(ት)፦ይ ህ አስታራቂው መንገድ ነው:: እንደ መጀመሪያው ጎራ ልቅነትና ሥርዓት አልበኝነት እንዳይበዛ በተቋማዊ ልጓም፣ እንደ ሁለተኞቹ ጎራ ቆሞ ቀርነት ሥር እንዳይሰድ በውድድር አለንጋ ሸንቆጥ በማድረግ ምጣኔሀብትን ከመክፈት የሚገኙ በረከቶችን ማብዛትና ጦሶችን መቀነስ ይቻላል ባይ ናቸው:: እንደ ሁለተኛዉ የጎመን ድስት ታቅፈው ክረምቱን ከርመው በጋዉን ለመባጀት አይዳዳቸውም:: እንደ መጀመሪያዉም " የጎመን ድስት ይዉጣ፣ የገንፎ ድስት ይግባ" ብለው በወረት አይገለበጡም:: የገንፎ ድስት ሲገባ የጎመን ድስት መውጣት አይጠበቅበትም:: ቢያሻዉ ቫይታሚኑን ለሚፈልጉ በዓይነትነት፣ካልሆነ ዘይት ለሚሹ በጎመንዘር መልክ ህላዌዉን ይቀጥላል:: ገንፎም የድርሻዉን ድስትና ቦታ ያገኛል:: "ጠርጥር፣ ከገንፎ ውሥጥ ይኖራል ስንጥር" እንደሚባለው መንግሥታዊ የምዘናን እና የቁጥጥር አሠራሮችን በጥንቃቄ በማዘመን ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ በማድረስ አጠቃላይ ያገር ሀብት እንዲዳብር፣ የሚፈጠረዉ ምርትና አገልግሎት አይነት በጥራትም በዓይነትም እንዲበዛ፣ አሰረጫጨቱ እንዲሳለጥ፣ ተወዳዳሪ አሳብ ያላቸው ድርጅቶች የወረት እጥረት እንዳያጋጥማቸው የብድር አቅርቦትን በማስፋፋት የጎላ አስተዋጽ እንዲያደርግ አለበት ::

በወረቀት ላይ የአንድ አገር ምጣኔሀብት ወይ ዝግ ወይ ክፍት ሊል ይችላል:: አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን ከሌላዉ ዓለም ጋር ምንም ዓይነት ንክክኪ ሳያደርግ የሚኖር ምጣኔ ሁብት የለምና ፍጹም ዝግ የሚባል የለም:: እንዲህም የተወሰኑ ዘርፎችን ሳገር ዉስጥ ይዞታነት በህግ ስለሚገድብ ባ ብሎ የተከፈተ ምጣኔሀብት በዓለም አይገኝም:: ምንም እንካን ደረጃዉ ቢለያይም ሁሉም የዓለም አገሮች ምጣኔ ሀብታቸው ገርበብ ተደርጎ የተከተፈተ ነው:: ከዚህ አንጻር ካየነው፣ ካልደፈረሰ አይጠራም የሚሉትም ሆኑ ጎመን በጤና የሚሉት እሩቅ የሚያስኬዱ አይደሉም::

በአብዛኛው ባዶ ድምር የጀማሪ ጨዋታ ነው::ጠጋ ብለን ካየነው ብዙው ነገር በብስለት ከተያዘና ከተስተናበረ ያንዱ መኖር የሌላዉን ህላዌ እንዲያከትም አያደርገውም:: ለስሙ " የጎመን ድስት ይዉጣ ፣ የገንፎ ድስት ይግባ ቢባልም" ብልጥ ሰው ገንፎዉን እና ጎመኑን ወይ በአንድ ድስት በየተራ ያበስላል ወይም ምድጃዉን አስፍቶ ድስቶቹን አብዝቶ ልዩ ልዩ ወጥ ይሰራል እንጂ፣ አንዱን ሲሸኝ አንዱን ሲቀበል አይኖርም::በ"ሐ" ጎራ ከሚነሱ አተያዮች አንፃር፣
(1) ከዉጭ ባንኮች መግባት ጋር አብረው የሚመጡ ጦሶች ቢኖሩም፣ እነሱን ተቋቁሞ በፍጥነት የሚያድግ የገንዘብ ዘርፍና ለአጠቃላይ ምጣኔ ሀብት ማበብ ፣ በተለይም በጊዜ ሂደት ጠቃሚ ነው ባይ ናቸው::
(2) ከዉጭ የሚመጣዉን ጫና ተቋቁመዉ ገበያዉ ላይ መቆየት የሚችሉ አገር በቀል የገንዘብ ተቋማት የሚቀስሙትን ተጨማሪ ልምድ ይዘው ወደ ሌላ አገራት አገልግሎታቸዉን የማስፋፋት ( በተናጠል ወይም ከየአካባቢዉ ባንኮች ጋር ሽርክና በመፍጠር) እና ተጨማሪ ገበያ የማግኘት እድል ይኖራቸዋል::
(3) ጊዜያዊ ቢሆንም እንኳ የዉጭ ባለሃብቶች ሲገቡ የዉጭ ምንዛሬ ፈሰስ ስለሚያደርጉ ላጭር ጊዜም ቢሆን የምንዛሪ እጥረት ይቀርፋሉ:: በጊዜ ሂደት ግን እነሱ በትርፍ መልክ የዉጭ ምንዛሪ ወዳገራቸው ስለሚወስዱ የነጠረ ጥቅማቸው የሚመዘነው አጠቃላይ ምጣኔሀብቱን አሳድገው የውጭ ምንዛሬ የማመንጨት አቅሙን እንዲጎለብት አስተዋፆ ካደረጉትና ከአገር ዉስጥ እየመጠጡ ወደ መቀመጫቻው ከሚልኩት ሀብት ተመዛዝኖ የሚገኘዉ ነው::

ነገሩን ለመቋጨት አንድ ድርጊት ጎጅም ጠቃሚም የሚሆነው መጥኖ በመጠቀምና ባለምጠቅም ነው:: እሳት ሲመጠን ያበስላል:: ሲበዛ ያቃጥላል:: ዉሃ ሲመጠን እና ሲመራ ይጠጣል፤ ለመስኖ ለሃይል ማመንጫ ይዉላል:: ከገደብ ሲያልፍ ጎርፍ ሁኖ ይወስዳል፣ ጥልቅ ሁኖ ያሰምጣል:: በዚህ ትይዩ የዉጭ ባንክ ስለገባ ስላልገባ የሚፈጠር በጎ ፍሬ የሚወሰነው አጠቃቀሙን ያወቅን እንደሆነ ነው( ባይገባ ያገር ውስጥ ባንኮች ገበያዉ ላይ ተግተው ሰርተው ሊለወጡ ይችላል:: ቢገባ አብዛኛዉ ቆጣቢና ተበዳሪ አማራጭ ያገኛል:: ቆጣቢ ሻል ያለ ወለድ፣ ተብዳሪው ዝቅ ያለ ያለ ወለድ ሊያገኙ ይችላሉ::) በቀጣይ የትኞቹ አገራት፣ መቼና በምን ደረጃ ምጣኔሁታቸዉን ለዉጭ የገበያ ተዋንያን በመክፈት ተጠቀሙ(ተጎዱ) የሚለዉን እናያለን:: ቸር ያሰንብተን

## 26ተኛው አዲስ ቻምበር አለም አቀፍ የንግድ ትርኢት የንግድ ማህበረሰቡን ምርቶች በማስተዋወቅና የንግድ ትስስር በመፍጠር ወሳኝ ሚና እንደነበረው ተገለጸ



**በስታፍ ሪፖርተር**

በየአመቱ የካቲት ወር አጋማሽ ላይ የሚካሄደው የአዲስ ቻምበር አለምአቀፍ ንግድ ትርኢት በአዲስ አበባ ኢግዚቢሽንና ገበያ ልማት ማእከል ከየካቲት 14 እስከ 18 2016 አ.ም ተካሄዷል:: በዚህ አምአቀፍ የንግድ ትርኢት በተለያዩ የምርት ዘርፎች የተሰማሩ የሃገር ውስጥ እና የውጭ ነጋዴዎች ተሳታፊ ሆነዋል:: ንግድ ትርኢቱን የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ተወካይ አቶ መከታ አዳፍሬ፤ የኢትዮጵያ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክርቤት ፕሬዝዳንት ኢንጂነር መላኩ እዘዘው እንዲሁም የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ በጋራ ያስጀመሩት ዝግጅት ነበር::

በወቅቱ በመክፈቻ ንግግር ከተሰሙት ንግግሮች መካከል የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ተወካይ አቶ መከታ አዳፍሬ ንግግር ይገኝበታል:: ንግድ እና ኢንዱስትሪ በመንግስት ትኩረት የተሰጠው ዘርፍ መሆኑን በንግግራቸው ያነሱት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ተወካይ ዘርፉ በበርካታ ችግሮች የተከበበ ቢሆንም መንግስት በመሰረተ ልማት፤በሎጀስቲክስ፤በቴክኖሎጂ እና በሌሎችም ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል::

በአዳዲስ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ስራዎች ላይ በመንግስት የተሰጠው ትኩረት ንግድን ለመከወን አወንታዊ ድርሻው ሰፊ መሆኑን በንግግራቸው ያነሱት የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ቢሆንም የግሉ ዘርፍ የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ አሁንም እገዛ እንደሚያስፈልገው ጠቁመዋል::

አክለውም ለቴክኖሎጂ እና አዳዲስ ፈጠራዎች መስፋፋት ለሚገጥሙ እንቅፋቶች የፖሊሲ ማሻሻያዎች ፤የባለድርሻዎች ተቀናጅቶ መስራት ችግሮቹን ለመቅረፍ እና ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንደሚያግዙ የገለጹ ሲሆን ለዚህ ደግሞ ንግድ ምክር ቤቱ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች እና የሚያዘጋጃቸው ንግድ ትርኢቶች እገዛ እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል::

ለአምስት ቀን የቆየው ንግድ ትርኢትም ተሳታፊዎች ራሳቸውን ለማስተዋወቅም ሆነ አዳዲስ አሰራሮችን እንዲቀስሙ እንዲሁም የገበያ እድሎችን ለማግኘት እድል እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል::